# ትንፋሽህ ሁልግዜ ማስታወሻችን ነው

የጥበቡ ምህዳር አውራ ኮኮብ ፀሀይ

የዜማችን ንጉስ ጥዑመ-ድምፅ ሰናይ

ትውልድ የወለደ ትውልድ ያዋለደ

ጥላሁን አረፈ እንጂ መች ርቆ ሄደ

እንደ ያሬድ ቅኝት እንደ ዳዊት ዜማ

እንደ እየሩሳሌም እንደ መካ መዲና

የሚሊዮኖች ታቦት መሳለሚያ ማማ

ሀውልት ነው ጥላሁን የልባችን ፋና

ያዜምክበት መስኮች የአዲሳባ አድባሩ

የክፍለ ሃገር ከተማ የገጠር መንደሩ

ድምጽህን ያስተጋቡት ተራራና ዱሩ

ፈርጥ ነህ ፍሬያቸው ልጃቸው የበኩሩ

ጥላሁን ራስ ዳሸን ሰማይ ያጣቀሰው

ጥላሁን ዓባይ ወንዝ ሞልቶ የማይነጥፈው

ጥላሁን የጥንቱ የዛሬው የነገው

አልፋና ኦሜጋ ግዜ የማይሽረው

**ትንፋሽህ ውስጣችን ምንግዜም ህያው ነው**

**ትንፋሽህ ሁልግዜ ማስታወሻችን ነው**

የአገር ፍቅር ልሳን ነው የወኔያችን ሞገድ
“በአጥንቴም ይከስከስ” የጻፍክልን አምድ
በእንባህ ያበሰከው ህዝብ ተርቦ ሲቸገር
አዳኝ መልእክተኛ  እንዳንተ ማን ነበር

አዜምን አብረንህ ጥልቀት ስፋቱን የእውነተኛን ፍቅር
“አንቺን ክፉ አይንካሽ” ነው ያልከንን ምስጢር
ዋለልን በውበት ኑዛዜ በ“ሞናሊዛዬ ነሽ” ጠማር
ነሆልለን በ“አረከ ፉኔ” ዋኘንበት በጥበብህ ባህር

አየነው ጥላሁን ሁሉኑም አየነው
የህይወትን ድራማ በዘፈንህ ቀዳነው
ማንነታችንን በአንተ ውስጥ ቃኘነው
አንተነትህን በእኛ ውስጥ ተማርነው

ጥላሁን ራስ ዳሽን  ሰማይ ያጣቀሰው
ጥላሁን ዓባይ ወንዝ ሞልቶ  የማይነጥፈው
ጥላሁን የጥንቱ  የዛሬም የነገው
አልፋና ኦሜጋ ግዜ የማይሽረው

**ትንፋሽህ ውስጣችን ምንግዜም ህያው ነው**
**ትንፋሽህ ሁልግዜ ማስታወሻችን ነው**

ጃዊሳ

April 2009

ለእውቁና ድንቁ ድምፃዊ ለጥላሁን ገሰሰ መታሰቢያ የተፃፈ;; አምላክ ለቤተሰቦቹ ጽናትን ለጥበቡ አፍቃሪዎች መጽናናትን ይስጥልን;;